አደረገው ፤ እነዚያንም ፡ ሰዎች ፡ እሳቱ ፡ ምንም ፡
አልነካቸውም ÷ የራሳቸውን ፡ ጠጕር ፡ አልለበ
ለባቸውም ÷ አላስጨነቃቸውም ።
፳፮ ያን ፡ ጊዜም ፡ እነዚያ ፡ ሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
በአንድ ፡ አፍ ፡ ፈጽመው ፡ አመሰገኑ ፤ በእሳት ፡
ጕድጓድ ፡ መካከል ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገ
ኑት ።
፳፯ የአባቶቻችን ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡
ይመስገን ፤ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለሙም ፡
የከበረ ፡ ነው ።
፳፰ የከበረ ፡ የጌትነቱ ፡ ስምም ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፤
የተመሰገነ ፡ ነው ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ የከበረ ፡
ነው ።
፳፱ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብለህ ፡ በምትመሰገንበት ፡
በጽርሐ ፡ አርያም ፡ አንተ ፡ የከበርህ ፡ ነህ ፤
ለዘላለሙ ፡ የተመሰገንህ ፡ ነህ ።
፴ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ ሆነህ ፡ የውቅያኖስ ፡ ጥልቆ
ችን ፡ የምታይ ፡ አንተ ፡ የከበርህ ፡ ነህ ፤ የተ
መሰገንህ ፡ ነህ ÷ ለዘላለሙም ፡ የከበርህ ፡ ነህ ።
፴፩ በጌትነትህም ፡ ዙፋን ፡ አንተ ፡ የከበርህ ፡ ነህ ፤
የተመሰገንህ ፡ ነህ ÷ ለዘላለሙም ፡ የከበርህ ፡
ነህ ።
፴፪ ከሰማዮች ፡ በላይ ፡ ባለ ፡ ሰማይም ፡ የተመሰገ
ንህ ፡ ነህ ፤ አንተ ፡ ለዘላለሙ ፡ ፈጽመህ ፡ የከ
በርህ ፡ ነህ ።
፴፫ እግዚአብሔር ፡ የፈጠራቸው ፡ ፍጥረቶች ፡
ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤
እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለሙም ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።
፴፬ ሰማዮች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤
እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለሙም ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።
፴፭ እግዚአብሔር ፡ የፈጠራቸው ፡ መላእክት ፡
እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤ እርሱ ፡
ለዘላለሙ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ከፍ ፡ ከፍ ፡
ያለም ፡ ነው ።
፴፮ ከሰማዮች ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ ውኃዎች ፡ ሁሉ ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤ ለዘላለሙ ፡
የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
፴፯ የእግዚአብሔር ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤ እርሱ ፡ ለዘላለም ፡
የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
፴፰ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ
ታል ፤ እርሱ ፡ ለዘላለም ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷
ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
፴፱ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ከከቦች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመ
ሰግኑታል ፤ እርሱ ፡ ለዘላለም ፡ የተመሰገነ ፡
ነው ÷ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
፵ የበጎ ፡ ጠል ፡ የበጎ ፡ ዝናም ፡ እግዚአብሔርን ፡
ያመሰግኑታል ፤ እርሱ ፡ ለዘላለም ፡ የተመሰ
ገነ ፡ ነው ÷ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
፵፩ ነፋሶች ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ
ታል ፤ እርሱ ፡ ለዘላለም ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷
ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።

እሳት ፡ ዋዕይ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፵፪
ታል ፤ እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለም ፡
ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
መዓልትና ፡ ሌሊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰ ፵፫
ግኑታል ፤ እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላ
ለም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
የክፉ ፡ ጠል ፡ የክፉ ፡ ጤዛ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፵፬
ያመሰግኑታል ፤ እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷
ለዘላለም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
ብርድ ፡ ውርጭ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፵፭
ታል ፤ እርሱ ፡ ለዘላለም ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷
ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
ብርሃን ፡ ጨለማ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፵፮
ታል ፤ እርሱ ፡ ለዘላለም ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷
ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
ደጋ ፡ ቆላ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤ ፵፯
እርሱ ፡ ለዘላለም ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
በረድ ፡ ጉም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤ ፵፰
እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለም ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
መብረቅ ፡ ደመና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፵፱
ታል ፤ እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለም ፡
ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
ምድር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመሰግነዋለች ፤ ፶
እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለም ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
ተራሮች ፡ ኮረብቶች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰ ፶፩
ግኑታል ፤ እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላ
ለም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚበቅሉ ፡ አትክልት ፡ ሁሉ ፡ ፶፪
እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤ እርሱ ፡ የተ
መሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡
ነው ።
ጥልቆች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤ ፶፫
እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለም ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
ባሕር ፡ ፈሳሾች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፶፬
ታል ፤ እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለም ፡
ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
በውኃ ፡ ውስጥ ፡ የሚመላለስ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ፶፭
እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤ እርሱ ፡ የተ
መሰገነ ፡ ነው ÷ ለዘላለም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡
ነው ።
በሰማይ ፡ የሚበሩ ፡ ወፎች ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብ ፶፮
ሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤ እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡
ነው ÷ ለዘላለም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
አራዊት ፡ እንስሳት ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፶፯
ያመሰግኑታል ፤ እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷
ለዘላለም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለም ፡ ነው ።
የአዳም ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፶፰
ታል ፤ እርሱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ÷ ከፍ ፡ ከፍ ፡
ያለም ፡ ነው ።
እስራኤል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ፤ ፶፱

